+Pass

DISCOVER MORE OPPORTUNITIES

እያንዳንዱ ልጅ ከአውቶቢስ መቼ እና የት እንደሚሳፈር እና እንደሚወርድ ማወቅ እጅግ አስፈላጊ ነው። በDPS ውስጥ ለመጓጓዣ (ለትራንስፖርት) ብቁ የሆነና ቢጫውን አውቶቢስ የሚሳፈር እያንዳንዱ ተማሪ ያለምንም ልዩነት የእሱን +Pass በየቀኑ እንዲጠቀም ይጠበቃል። ለምትክ ወይም ጊዜያዊ ይለፍ፣ የት/ቤትዎን ጽ/ቤት ወይም በሳምር ወራት የትራንስፖርት አገልግሎትን ያነጋግሩ።

**ስለ የጉዞ መስመሮች እና ጊዜ ሰሌዳዎች ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት transportation.dpsk12.org ይጎብኙ። በድንገተኛ ጊዜ ት/ቤቱ ይነገረው እና ወላጆችን/ተማሪዎችን በቀጥታ ያነጋግራል።**

## +PASS እንዴት ይሠራል

1. ተማሪዎች ወደ/ከ አውቶቢስ ሲሳፈሩ እና ሲወርዱ የእነሱን +Pass የካርድ ማንበቢያው ላይ ያስቀምጣሉ።
2. የካርድ አንባቢው መነበቡን ለማረጋገጥ ቢጽ የሚል ድምጽ በማሰማት አረንጓዴ ያበራል።
3. ተማሪዎች ወደ/ከ ት/ቤቱ አውቶቢስ የሚሳፈሩበት እና የሚወርዱበት ጊዜ፣ ቀን እና ቦታ ወዲያውኑ በትራንስፖርት ጽ/ቤቱ እና በት/ቤቱ ኃላፊዎች ብቻ በሚታይ ዳታቤዝ ይመዘገባል።

## ምትክ እና ጊዜያዊ +PASS

- የጊዜያዊ ይለፍ ከት/ቤቱ አገልግሎት መስጫ ጽ/ቤት (ፍሮንት ኦፊስ) የሚሰጥ ሆኖ ቢበዛ ለአምስት ቀናት ብቻ የሚያገለግል ይሆናል። ትክክል የሆነ ምትክ +Pass መያዝ አለበት።
- የጠፋ +Pass ምትክ ለማግኘት የት/ቤቱን አገልግሎት መስጫ ጽ/ቤት (ፍሮንት ኦፊስ) ያነጋግሩ።

## አቅርቦቶች

- የት/ቤት ጽ/ቤት፡- ት/ቤቶች የመጀመሪያ የግንኙነት ነጥቦች ናቸው፤ እነሱም የተማሪ አውቶቢስ መረጃን በኢንፋይናት /Infinite/ ግቢ ውስጥ ሊያረጋግጡ ይችላሉ።
- የአውቶቢስ ስርጭት፡- (720) 423-4624 (ከ5:30 ሌ ኤም – 7:30 ፒ ኤም)
  - አሁቶቢስ ከ15 ደቂቃ በላይ ዘግይቷል
  - ተማሪ አልተሳፈረም
  - ተማሪዎች ጎድለዋል
  - ወድቀው የተገኙ እቃዎች

  የDPS ደህንነት እና ፀጥታ፡- 720423-3911
  robin_greene@dpsk12.org
  (ከ7:30 ፒ ኤም በኋላ ወይም በድንገተኛ ጊዜ)
- መጓጉዣ (ትራንስፖርት)፡- 720423-4600
  robin_greene@dpsk12.org
  - የአውቶቢስ መስመሮች መረጃ
  - የ+Pass ጥያቄዎች
  - አጠቃላይ መረጃ
- Safe2Tell®: 1 (877) 542-SAFE
  የተማሪ የደህንነት ስጋቶችን/ጭንቀቶችን ሪፖርት ያድርጉ
- የወላጆች መዳረሻ (ፖርታል)፡- myportal.dpsk12.org
  ወላጆች አሁን የሚከተሉትን ጨምሮ ጠቃሚ መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ፡-
  - የአውቶቢስ መስመር ዝርዝር (የአውቶቢስ ማቆሚያ ቦታ (ፌርማታ) እና ጊዜዎች)
  - የ+Pass ካርድ አጠቃቀም
  - ጠቃሚ የማጓጓዥ/ትራንስፖርት ወቅታዊ መረጃዎች

  በወላጅ ፖርታል ለመመዝገብ ት/ቤትዎን ያነጋግሩ

## ተማሪዎች፡-

- ሁሉም ተማሪዎች +Pass ን በየቀኑ መጠቀም አለባቸው
- ወደ/ከ አውተቢሱ ሲገቡ እና ሲወጡ +Passዎን ይቅረጹ
- ተማሪዎች ለይለፋቸው (+Pass) ተጠያቂዎች ናቸው። ካርዳችሁን እንዳታኙኩት፣ እንዳትቀዱት ወይም እንዳትጥሉት።

ለበለጠ መረጃ ደረ ገጻችን፡- transportation.dpsk12.org/pass ይጎብኙ።

## ወላጆች፡-

- ልጆችዎ የ+Pass ካርዳቸውን በአውቶቢስ ሲሄዱ ሁሌም መጠቀማቸውን ያረጋግጡ።
- በድንገተኛ ጊዜ +Pass መጓጓዣን (ትራንስፖርቴሽንን) መጠቀም ያስችላል፣ ለት/ቤቶችም የትኞቹ ተማሪዎች በአውቶቢሱ ውስጥ እንዳሉ ለማወቅ ያስችላቸዋል።
- +Pass ለDPS ደግሞ ሀብትን/አቅርቦትን በተሻለ መንገድ ለመጠቀም እና ከወላጆች ጋር የተሳለጠ ግንኙነት (ኮሚዩኒኬሽን) እንዲያደርግ ያስችለዋል።

## የብቁነት መሥፈርት

የትራንስፖርት አገልግሎት የሚገኘው በትምህርት ቦርድ በተዘጋጅ የብቁነት መሥፈርት መሠረት ነው።

- **የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት፡-** ከኬጂ እስከ 5ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች የተመዘገቡ እና ከአጎራባች ት/ቤታቸው ከአንድ ማይል ርቀው የሚኖሩ መሆን አለባቸው።
- **መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት፡-** ከ6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች የተመዘገቡ እና ከአጎራባች ት/ቤታቸው 2.5 ማይል ርቀው የሚኖሩ መሆን አለባቸው።
- **የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፡-** ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ እና ከአጎራባች ት/ቤታቸው 3.5 ማይል ርቀው የሚኖሩ ተማሪዎች በRTD ይለፍ /pass/ መርሃ-ግብር ለመሳተፍ ብቁ ናቸው።

ማስታዎሻ፡- መጓጓዣ (ትራንስፖርት) ዋስትና የለውም ይህ በተለይ ወላጆች በየአመቱ የት/ቤት ምርጫ የምዝገባ ሂደት ስለሚያልፉ በጣም ጠቃሚ ነው።

### ልዩ ሂደት /EXCEPTION PROCESS/

አንድ ተማሪ የአውቶቢስ መጓጓዣ (ትራንስፖርት) ቢፈልግ ነገር ግን በትምህርት ቦርዱ የተቀመጡትን የብቁነት መሥፈርቶች ባያሟላ የልዩ መጓጓዣ (ትራንስፖርት) ቅጹን ይሙሉ። ቦታ ካለ ልዩ አስተያየት ተደርጎ እድሉ ሊሰጠው ይችላል። ቅጹ በመስመር ላይ ከ transportation.dpsk12.org/eligibility ይገኛል። ለተጨማሪ ጥያቄ በ(720) 423-4699 ይደውሉ (ከሰኞ እስከ አርብ፣ 8 ሌ ኤም እስከ 3 ፒ ኤም)።

# ስለአውቶቢስ ጠቃሚ መረጃ

## ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን በፊት

- የአውቶቢስ መስመር መረጃን ይከልሱ (የጧት እና የከሰዓት ሁለቱንም)
- የአውቶቢስ መስመር ቁጥሩን ያስታውሱ
- የአውቶቢስ መነሻ እና መምጫ ሰዓቶችን ይወቁ
- የአውቶቢስ ማቆሚያ ቦታ(ዎችን) ወይም ፌርማታ(ዎችን) ይጎብኙ
- ለአውቶቢሱ ሠራተኞች ራስዎን ያስተዋውቁ

## ወደ አውቶቢስ ማቆሚያው (ፌርማታው) ለመድረስ

- የአውቶቢስ ማቆሚያ ቦታው (ፌርማታው) ከ10 ደቂቃ በፊት ቀድማችሁ ድረሱ
- ወደ ፌርማታው ሲሄዱ እና ሲመለሱ ከአደጋ የፀዳውን መንገድ ያዙ
- እንግዳ ሰዎችን አታናግሩ ወይም ልውሰዳችሁ ቢል እሺ እንዳትሉ!
  እንግዳ ሰው ከቀረባችሁ፣ ቶሎ ብላችሁ ለአውቶቢሱ አሽከርካሪው አሳውቁ
- በተመደበላችሁ ፌርማታ እና ሰዓት ወደ አውቶቢሱ ተሳፈሩ
- አውቶቢሱ ጥሎዎት ከሄደ ወይም ከ15 ደቂቃ በላይ ከዘገየ በሥ.ቁ. (720) 423-4624 ይደውሉ
  - **ማስታወሻ:-** የመጀመሪያዎቹ ሁለት የትምህርት ሳምንታት፣ በበረዷማ ቀናት፣ ወይም በትራፊክ መጨናነቅ አውቶቢሶች ሊዘገዩ ይችላሉ

## አውቶቢስ ፌርማታ ላይ

- በአውቶቢስ ፌርማታ ዙሪያ ያሉ ንብረቶችን ጠብቁ በአትክልቶች ሥፍራ ላይ ቆሻሻ እንዳትጥሉ ወይም እንዳትጠቀጥቋቸው
- ለመሳፈር ዝግጁ ሁኑ፣ እንዲሁም ከዋና መንገድ/ከመንገድ ጠርዝ ርቃችሁ በጥንቃቄ ቁሙ
  - **ማስታወሻ:-** የአውቶቢሱ ሾፌር አውቶቢሱ ደርሷል ብሎ እናንተን ለማንቃት ጡሩንባ (ክላክስ) ሊነፋ አይችልም። በሰዓቱ ተገኙ
- ከአደጋ ክልሎች ራቁ (ከዚህ በታች ያለውን ምስል ተመልከቱ)
- ለመሳፈር የየራሳችሁን+Pass ዝግጁ አድርጋችሁ ያዙ

## ወደ አውቶቢስ መሳፈር

- ሁሉም ተማሪዎች የየራሳቸውን +Pass በየቀኑ መጠቀም አለባቸው!
- ወደፊለፊት ዞራችሁ እንደተቀመጣችሁ ቆዩ
- እግሮቻችሁን ከመተላለፊያ መስመሩ ውጭ አድርጉ
- ሁሉንም የሰውነትዎ አካላት አውቶቢሱ ውስጥ ያድርጉ
- መቀመጫ ወንበሮችን ለሌላ ሰው አይያዙ
- በአውቶቢስ ላይ ሲጓዙ ሾፌሩን ላለመረበሽ ድምጻችሁን ቀንሱ
- ትላልቅ እና አደጋ ሊያከትሉ የሚችሉ እቃዎችን ወደ አውቶቢሱ ይዞ መግባት የተከለከለ ነው
- የስኬት መንሸራተቻ (ስኬትቦርድ) እና የእስፖርት እቃዎች ሙሉ በሙሉ በሻንጣ ውስጥ መከተት አለባቸው

## ከአውቶቢስ መውረድ

- ተማሪዎች ከአውቶቢስ ሊወርዱ የሚችሉት በተመደበላቸው ፌርማታ ብቻ ይሆናል
- ]የተለየ የመውረጃ ቦታ ከተፈለገ ከወላጆች እና ከት/ቤት አስተዳደር የጽሑፍ ፈቃድ ማቅረብ አለባቸው
- አውቶቢሱ መሉ ለሙሉ እስኪቆም እና በሩ እስኪከፈት ድረስ ቁጭ ብላችሁ ጠብቁ

## ልዩ መመሪያዎች

- **የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች:-** ተማሪው ብቻውን ሊለቀቅ አይችልም የሚል መመሪያ ለሾፌሩ በተሰጠበት ሁኔታ ወላጁ፣ አሳዳጊው ወይም ሌላ የተመደበ አዋቂ ሰው አውቶቢሱ ድረስ መምጣት እና ልጁን መቀበል አለበት።
- ሁሉም የግማሽ ቀን የመዋዕለ ህፃናት እና የቅድመ-መደብኛ ትምህርት ተማሪዎችን የታወቀ/የተፈቀደለት አሳዳጊ ሊቀበላቸው ይገባል። በቀኑ መጨረሻ ላይ የሚለቀቁ የመዋዕለ ህፃናት ተማሪዎች ከታላቅ ወንድም/እህት ጋር ወይም ከታወቀ/ከተፈቀደለት አዋቂ ሰው ጋር በተመደበው ፌርማታ ላይ እንዲወርዱ ይደረጋል እንጂ ብቻቸውን አይለቀቁም።
- ብቻቸውን ሊለቀቁ የማይችሉ እና ሊወስዳቸው የሚችል አዋቂ ሰው ያልመጣላቸው ልጆች በአውቶቢሱ ውስጥ በመቅረት አብረው በመስመሩ መጓዛቸውን ይቀጥላሉ። በስተመጨረሻም ወደ አውቶቢስ መጨረሻ ማቆሚያ ሊወሰዱ ይችላሉ።

## በአውቶቢስ ላይ የተማሪዎች ሥነ-ምግባር

- አክብሮት ይኑራችሁ፣ መልካም ቃላትን ተጠቀሙ፣ ለደህንነታችሁ ቅድሚያ ስጡ
- **ከፍተኛ የሆነ የሥነ-ምግባር ግድፈቶች:-** ከፈተኛ የሥነ-ምግባር ግድፈቶች አጸያፊ/አላግባብ ንግግር፣ መደባደብ/አካላዊ ጠብ አጫሪነት፣ ትንኮሳ/ማሸማቀቅ፣ ንብረት ማበላሸት/አውዳሚነት፣ ሌብነት፣ ሴሰኛ ባሕርይ፣ ከአውቶቢሱ ሠራተኞች ጋር መጋጨት የሚሉት ይገኙባቸዋል።
- **ታናናሾችን ማሸማቀቅ:-** በDPS ታናናሾችን ለሚያስገድዱ እና ለሚያሸማቅቁ ምንም ትዕግስት የለም። አንድ ተማሪ በሌላ ተማሪ ከተሸማቀቀ ወይም ፍርሃት ከተሰማው፣ የሚፈራውን/የሚጠላውን ነገር ለአውቶቢሱ ሾፌር ወይም ረዳት በቀጥታ ማሳወቅ አለበት።

የትራንስፖርት አገልግሎቱ የከትምህርት ሰዓት በኋላ እና ልዩ የአውቶቢስ ተጠቃሚ ተማሪዎችን ወይም እጅግ የከፋ ሥነ-ምግባር የሚያሳዩ ተማሪዎችን በአውቶቢሱ ውስጥ ለሌሎች ተማሪዎች አደጋ ሥጋት ሊሆኑ በሚችሉበት ጊዜ አውቶቢስ እንዳይጠቀሙ የማገድ መብቱ የተጠበቀ ነው። ተማሪዎቹም አግባብ ባለው የቦርድ ፖሊሲ መሠረት በት/ቤቱ ቅጣት ሊጣልባቸው ይችላል።

## አማራጭ መጓጓዣ (ትራንስፖርት)

- **በብስክሌት ወደ ት/ቤት መሄድ:-**
  - ሄልሜት እና የአደጋ መከላከያ አልባሳት ልበሱ
  - በቀኝ በኩል/እንደ ትራፊኩ አቅጣጫ ንዱ
  - ግራ እና ቀኛችሁን ተመልከቱ
  - በቀጥታ መስመር ንዱ
  - ወደ ሌላ መንገድ ከመግባታችሁ በፊት (የያዛችሁት መንገድ መጨረሻ ላይ) ቆም በሉ
- **በእግር ለመሄድ:-**
  - አንድላይ ተጓዙ
  - የምትታዩ ሁኑ
  - ግራ እና ቀኛችሁን ተመልከቱ
  - መንገዱን በእግረኛ መንገድ ማቋረጫው ብቻ እና ብቻ አቋርጡ፣ ስትሄዱም ሁልጊዜም የእግረኛ መንገዱን በመጠቀም ይሁን
  - ለትራፊክ ምልክቶች፣ ማስጠንቀቂያዎች እና የት/ቤት ትራፊክ ፖሊሶች ታዛዥ ሁኑ




### ቁም! ሕጉ ነው!

- ብልጭ ብልጭ የሚሉ መብራቶች ቁም/አቁም ማለት ናቸው
- ልጆች አሉ
- ቀዩ መብራት ብልጭ ብልጭ ማለቱን እስኪያቆም ድረስ እንዳትሄድ/ጂ